# ትንቢተ ዳንኤል ጥናት(35)

## ጥናት አንድ የመግቢያ ጥናት

1. ትንቢተ ዳንኤል በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የመግባቱን ትክክለኛነትና በጌታ በየሱስ ተቀባይነት እንዳለው የሚያሳየን በማቴዎስ መጽሃፍ ውስጥ የትኛው ክፍል እንደሆነ ተናገር፡፡
2. በማቴ 24፡15-16 ላይ በተለይም ‹‹አንባቢው ያስተውል›› የሚለው አነጋገር ስለ ትንቢተ ዳንኤል መጽሃፍ ሊኖረን ስለሚገባን አመለካከት ምን ትረዳለህ? አንተስ ይህንን ለማድረግ ምን ያህል ልብህንና ሁለንተናህን አዘጋጅተሃል?
3. ዳንኤል አገልግሎቱን ያገለገለባቸው ነገስታት ቁጥር ስንት ነበሩ? ስማቸውን እነማን እንደነበሩ ተናገር፡፡ ለሰባ አመታት በነዚህ ነገሥታት ስር በታማኝነትና በቅድስና ሲያገለግል መቆየቱ ምን ያስተምረናል?
4. ዳን 2 ላይ ናቡከደነጾር የምድርን ነገሥታት በተለያዩ ለውበትና ለጌጥ ሰዎች በሚያገለግሉ ነገሮች አምሳል ሲያይ፤ በምዕ 7 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ለዳንኤል የምድርን ነገስታት በክፉና በአስፈሪ አራዊት መስሎ በማሳየቱ እግዚአብሄር ሊያስተምረን ያለው ነገር ይመስልሃል ወይ? ከሆነስ ከዚያ የምትማረው ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
5. ዳን 2፡37-44 ላይ የሚታየውን የህልም ፍቼ ከሉቃ 21፡24 ጋራ በማገናዘብ በተለይም ‹‹የአህዛብ ዘመን›› የሚለውን ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ፡፡ የአህዛብ ዘመን የጀመረው መቼ ነው ትላለህ? ማብቂያውስ መቼ ይሆናል?

# ጥናት ሁለት ዳን 1፡1-10

የጥናት ዓላማ፡- በአስቸጋሪና ሁኔታዎች ውስጥ ስንገኝ ያለሁበትን ሁኔታ ጌታ ያውቃል በማለት የስንፍና ህይወት እንድንኖር፤ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ስሙን በአህዛብ ፊት ማስከበር እንደሚጠበቅብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ዳንኤል ግን በንጉሱ ምግብና የወይን ጠጅ እንዳይረክስ ወሰነ›› ›› ዳን 1፡2

1. ዳን 1፡1-10 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-2ትን ስናነብ ኢየሩሳሌምን የከበበው ንጉስ ስም ማን ይባላል? ኢየሩሳሌም ስትከበብ የይሁዳ ንጉስ ማን ነበረ?
2. 2ኛ ነገ ምዕ 24 ቁ2‹‹እግዚአብሄር…ላከበት›› ‹‹በእግዚአብሄር ቃል መሰረት›› ቁ3 ‹‹እግዚአብሄር ባዘዘው መሰረት›› የሚሉትን አነጋገሮች ስንመለከት ስለይሁዳ ወደ ምርኮ መወሰድ በእርግጠናነት መናገር የምንችለው ነገር ምንድነው? 2ኛ ነገ 24፡3-4 በዚህ ሁሉ የምናሴ አስተዋጽኦ ምን ነበረ?
3. ቁ2 ስንመለከት፤ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄምና በእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ የነበሩት ኢቃዎች በባቢሎን ንጉስ እጅ የወደቁት በምን መንገድ ነበረ? ለምንድነው እግዚአብሄር  ህዝቡንና የመቅደሱን ዕቃ ለምርኮ አሳልፎ መስጠት የነበረበት? ዘዳ 28፡1 28፡15 28፡49-52 ትን አንብብ፡፡
4. በዳን 1፡3-5 መሰረት የንጉሱ የጃንደረቦች አለቃ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲያደርግ የታዘዘው ትዕዛዝ ምን ነበረ? ከዚሁ ትዕዛዝ ጋር በተጨማሪነት የተሰጡትን ቢያንስ ስምንት መለኪያና ሚዛኖች ተናገር፡፡
5. ይህ አስፉኔዝ የተባለው ሰው በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የታዘዘው ሌላ ትዕዛዝ ምን ነበረ? ቁ4-5ትን ስትመለከት እነዚህን ሰዎች በዘመናችን አነጋገር ምን ሊያደርጋቸው ነው ናቡከደነጾር እየሞከረ ያለው?
6. ከንጉሥ ገበታ ለመብላትና ለመጠጣት፣ የተለየ ስልጠና ለመውሰድ ከታጩት መሃል በዚህ ክፍል የምናያቸውን አራት ሰዎች የአገር ቤት ስማቸውን ተናገር፡፡ እነዚህ ሰዎች የምርኮ አገር ስማቸው ማን ማን እንደሚባልም ተናገር፡፡ አዲስ ስም ያወጣላቸው ማን ነበረ?
7. ዳን 4፡8 ስታነብ የዳንኤል ስም ‹‹ብልጣሶር›› ተብሎ የተቀየረው ከምን ጋራ በተያያዘ ነበረ? ዳንኤል ማለት ‹‹እግዚአብሄር ፈራጄ›› ማለት ነው፡፡ ብልጣሶር ተብሎ በመጠራቱ ዳንኤል ወይም ጓደኞቹ ሲቃረኑ እናያለን ወይ? ዳንኤልን እንዲቀየር ሲጠይቅ የሚናየው አንድ ነገር ምንድነው? ከዚህ ምን መማር እንችላለን?
8. ዳንኤልና ጓደኞቹ ለምንድነው ከንጉሱ ገበታ የሚገኘውን ምግብና ወይን ጠጅ ላለመብላት የወሰኑት?  በምርኮ አገር በአህዛብ መሃል እየኖሩ ነገር ግን ልክ በኢየሩሳም በእግዚአብሄር ከተማ እንደሚኖሩ ሆነው ህይወታቸውን መምራታቸው ለአንተ ምን ያስተምርሃል? በማይመች ሁኔታ ውስጥ መገኘትህ የእግዚአብሄርን ቃል ላለመታዘዝና በሃጥያት ለመኖር ምክንያት አድርገህ ልትጠቀምበት አይገባህም፡፡

# ጥናት ሶስት ዳን 1፡11-21

የጥናት ዓላማ፡- በማይመች ሁኔታ ውስጥ እንኳን እያለ ስሙን ለማስከበር ለቆረጠና ታማኝ ሆኖ ለመኖር ለወሰነ አማኝ እግዚአብሄር በጊዜው አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ጸጋና በረከት እንደሚሰጥ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እግዚአብሄር ለእነዚህ አራት ወጣቶች በማንኛውም ስነ ጽሁፍና ትምህርት እውቀትና ማስተዋልን ሰጣቸው፤ ዳንኤልም ማንኛውንም ራዕይና ህልም የመረዳት ችሎታ ነበረው፡፡›› ዳን 1፡17

1. ዳን 1፡11-21 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ11-14 ላይ ስማቸው በግልጽ ያልተጠቀሱትንም ጨምሮ የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ዘርዝር፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የዳንኤል ጥያቄ ምን ነበረ?
2. የዳንኤል ጥያቄውን በምን ዓይነት ነው ያቀረበው? እምነት ያለውና እግዚአብሄርን ቢተማመን ኖሮ በድፍረት የእናንተን ምግብ አንበላም አትክልትና ውሃ ስጡን፤ ያለበለዚያም እግዚአብሄር ይመግበናል ማለት ነበረበት፤ በሚለው አነጋገር ትስማማለህ ወይ? ለምን? ከዳንኤል አቀራረብ ምን ትማራለህ?
3. ቁ13-15ትን በማንበብ በተለይም በቁ13 ላይ ዳንኤል የተናገረው ነገር የእምነት ንግግር ሊያሰኘን የሚያስችለን ነገር ምንድነው? አራቱ ጓደኞች በእግዚአብሄር ላይ መታመናቸው እንዳላሳፈራቸውስ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? አንተስ ዛሬ እንደነ ዳንኤል በእግዚአብሄር ላይ ሊያወራርደ የሚያስችል እምነትን አዳብረሃል ወይ?
4. መጋቢው ለነዳንኤል የንጉስን ምግብ ትቶ አትክልትና ውሃ እንዲሰጥ ያሳመነው ነገር ምን ነበረ? እዚህ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ የሆነበትን ምክንያት የሚጠቁም በቁ15-16 ውስጥ አንድ ቃል ምረጥ ብትባል የትኛውን ቃል ትመርጣለህ? ለምን?
5. ‹‹ንጉሱ የወሰነው ጊዜ ሲደርስ›› ይህ ንጉሱ የወሰነው ጊዜ ሲባል ምን ማለት ነው? ንጉሱ እነዚህ አራት ጓደኞችን የመሰለ እንደሌለው ንጉሱ የተገነዘበው በምን መንገድ ነው? ንጉሱ ያነጋገረው አራቱን ጓደኞች ብቻ እንዳልሆነ የሚያስገነዝበን ቃል የትኛው ነው?
6. በቁ20 ንጉሱ የጥበብና የማስተዋል ብልጫ ያላቸውን ለማወቅ የተጠቀመበት መንገድ ምንድነው? እነዳንኤል የተወዳደሯቸው ሰዎች ቁጥር ምን ያህላል ተብለህ ብትጠየቅ መልስህ ምንድነው?
7. ሉቃ21፡12-15 ሲታይ በኢየሱስ አመለካከት ወደ ነገስታትና ወደ ገዢዎች ፊት የመቅረብ ሁኔታ ሲፈጠር እኛ ሊኖረን ስለሚገባው አመለካከት ምን ይነግረናል? በዚህ ዓይነት አመለካከት ራሳችንን ስናስታጥቅ እግዚአብሄር ደግሞ በራሱ በኩል ሊያደርግ ስላለው ነገር የገባው ቃል ኪዳን ምንድነው?
8. በእነዚህ አራት ጓደኞች ህይወት ይህ ጌታ በሉቃስ ወንጌል የገባው ቃል ተፈጻሚ ሆኗል የሚያሰኘን ከዳን 1፡17-20 ውስጥ የትኛው ጥቅስ ነው? በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተህ ምስክርነትህን ለመጠበቅ ቆራጥ ውሳኔ ያደረግህበትና እግዚአብሄርም ውሳኔህን አክብሮ ካንተ ጋራ ሲቆም ያየህበት ሁኔታ ካለ ለወገኖች አካፍል፡፡ የታመኑበትን ጌታ አያሳፍርምና ሁኔታዎች ሲከፉ አታመቻምች፡፡

# ጥናት አራት ዳን 2፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ማናቸውንም ዓይነት የጸጋ ስጦታ ለሰዎች ሲሰጥ ከእርሱ ጋራ ህብረትና ግንኙነታችንን አጥብቀን ሌሎችን የምናገለግልበት መሳሪያ እንጂ፤ በመንፈሳዊ ነገር የላቅን መሆናችንን ለሌሎች የምናረጋግጥበት የግል መሳሪያ እንዳልሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የሰማይ አምላክ ምህረት ያደርግላቸውና ምስጢሩን ይገልጥላቸው ዘንድ እንዲጸልዩ አሳሰባቸው፡፡ ለዳንኤልም ምስጢሩ በሌሊት በራዕይ ተገለጠለት፡፡›› ዳን 2፡18-19

1. ዳን 2፡1-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በ2፡1-3 ንጉሱ ናቡከደነጾር የሆነውንና ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ ዘርዝር፡፡ይህ ንጉስ ስለሆነው ነገር በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ላስጠራቸው ሰዎች ስለሆነው ነገር የነገራቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. ወደ ንጉሱ የተጠሩት ሰዎች በቁ4-7 ላይ ህልሙን ለመፍታት ከንጉሱ የጠየቁት ምን ነበረ? ንጉሱ በቀ5 ላይ ከኮኮብ ቆጣሪዎቹ ምን እንደሚጠብቅባቸው ነው የሚነግራቸው?
3. በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ስናይ ሰዎቹ የተጠየቁትን ማድረግ ቢችሉና ወይም ባይችሉ ስለሚገጥማቸው ነገር የተነገራቸው ነገር ምን ነበረ? ኮከብ ቆጣሪዎቹ ለሁለተኛ ጊዜ ንጉሱን የጠየቁት ጥያቄ ምን የሚል ነበረ?
4. ቁ7-9 ሰዎቹ በመጀመሪያ የጠየቁትን ያንኑ ጥያቄ ደግመው መጠየቃቸውን ንጉሱ የወሰደው በምን ዓይነት ነው? ንጉሱ ፍቺውን አስመልክቶ የነበረው ፍርሃት ምን ነበረ? ናቡከደነጾር አገልጋዮቹ ትክክለኛ ትርጉም እንደነገሩት እርግጠኛ መሆን የሚችለው ሰዎቹ ምን ማድረግ ሲችሉ ነው?
5. በቁ10-12 ላይ ኮከብ ቆጣሪዎቹ ለንጉሱ አስረግጠው የነገሩትን ቢያንስ ሶስት ነገሮን ተናገር፡፡ ከነዚህ ሰዎች ሃሳብ ጋራ ምን ያህል ትስማማለህ? ለምን?
6. 12-13 ባለው ክፍል የተካሄደውን ነገር በራስህ ቃላት በአጭሩ ተናገር፡፡ በ14-16 ዳንኤል ያደረጋቸውን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ዳንኤል ካደረጋቸው ነገሮች ውስጥ ለእኛ ትምህርት ሊሆንልን የሚችል ብለህ የምታምነውን ለወገኖች አካፍል፡፡
7. ዳንኤል ወደቤቱ ተመልሶ ያደረገው የወሰዳቸው ሁለት እርምጃዎች ምንና ምን ነበሩ? ዳንኤል ነገሩን ለጓደኞቹ ገልጦ ሳያበቃ ወደ ጸሎት እንዲሄዱ ማድረጉ ምን ያስተምረናል?
8. ቁ19-23 በዳንኤል ምስጋና ላይ እግዚአብሄር እንደሚያደርግ ቢያንስ ስድስት ነገሮችን ዘርዝር፡፡
9. በዳን 1፡17 ላይ ‹‹ዳንኤል ማንኛውንም ራዕይና ህልም የመረዳት ችሎታ ነበረው›› በ2፡18-19 ላይ የዚህ አይነት ስጦታ ያለው ሰው በመሃላቸው እያለ ዳንኤልና ጓደኞቹ ህልሙን ለመተርጎም ወደ እግዚአብሄር ሲጸልዩ እንመለከታለን፡፡ ከዚህ ድርጊታቸው ስጦታን አስመልክቶ ምን ትማራለህ? መንፈሳዊ ስጦታ ምንጊዜም ቢሆን የባለቤቱ የእግዚአብሄር እንደሆነ መረዳት፣ እንዲሁም ፍሬአማ አገልግሎት ለማገልገል ቁልፉ ከሰጪው ጋራ ግንኙነትና ህብረት ማድረግ እንደሆነ መዘንጋት አያስፈልግም፡፡

# ጥናት አምስት ዳን 2፡24-49

የጥናት ዓላማ፡- ዛሬ ምንም ያህል ትልቅና የሚያስፈሩ ሆነው የምናያቸው መንግስታትና ነገስታት በሙሉ፤ አንድ ቀን በነገስታት ንጉስና በጌቶቹ ጌታ ሁሉም እንደሚደቁና እርሱም ለዘለዓለም የማይፈርስ ወይም ደግሞ ለሌላ ህዝብ አልፎ የማይሰጥን መንግሥቱ እንደሚመሰርት ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹በነዚያ ነገሥታት ዘመን፤ የሰማይ አምላክ ፈጽሞ የማይፈርስና ለሌላም ህዝብ የማይሰጥ መንግሥት ይመሰርታል፤ እነዚያን መንግሥታት ሁሉ ያደቃል፤ እስከመጨረሻውም ያጠፋቸዋል፤ ይህ መንግስት ራሱ ግን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል፡፡›› ዳን 2፡44

1. ዳን 2፡24-49 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ24-25 ላይ ዳንኤል አስቀድሞ እግዚአብሄርን ካመሰገነ በኋላ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ዳንኤል ወደ አርዮክ ራሱ የመጣ ሆኖ እያለ በንጉሱ ፊት ቀርቦ ‹‹አግኝቻለሁ›› በማለት ስለተናገረው ነገር ምን እንደምታስቡ ተወያዩበት፡፡
2. ቁ27-29ን ስናነብ ዳንኤል የንጉሱን ጥያቄ አስመልክቶ ከሌሎቹ ኮከብ ቆጣሪዎች ጋራ የሚስማማበት ሃሳብ ምንድነው? ይህንን አስመልክቶ በዳንኤልና በእነርሱ መሃል የምናየው ትልቁ ልዩነት ምንድነው ትላለህ?
3. እግዚአብሄር የህልሙን ምስጢር ስለገለጠት ምክንያት ዳንኤል በቁ29-30 ምን ይነግረናል? በዚህ ክፍል ስለዳንኤል የሚታይህ አንድ ግሩም ባህርይ ምንድነው?
4. በቁ31-35 ላይ ንጉሱ ያየው ምስል ምን እንደሚመስል አስረዳ፡፡ ምስሉን በማየት ላይ እያለ የሆነው ነገር ምን ነበረ? የምስሉ መጨረሻ ምን እንደሆነ ነው የሚነግረን?
5. ምስሉን ያደቀቀው የድንጋዩ አመጣጥ ከየት ነበረ? የድንጋዩስ መጨረሻ ምን ሆነ?
6. ቁ36-38 ላይ ዳንኤል ‹‹እንናገራለን›› በማለት በብዙ ቁጥር የሚናገርበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? ከዚህ አነጋገሩ ምን ትማራለህ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ‹‹ሰጥቶሃል›› ‹‹አድርጎሃል›› ሲል በቁ21 ላይ ዳንኤል ከጸለየው ጸሎት ጋራ እንዴት ይስማማል?
7. በቁ36-43 ዳንኤል ትርጉሙን ሲናገር ናቡከደነጾር በምስሉ ላይ በምንድነው የተመሰለው? ከብር እንዲሁም ከናስ ስለተሰሩት መንግስታት የተነገረውስ ምንድነው? ስለአራተኛው መንግስት በቁ40-43 ጠቃሚ የምትላቸውን ሃሳቦች ተናገር፡፡
8. በቁ46-49 ላይ የህልሙ መፈታት ያስገኛቸው ሁለት ግልጽ የሆኑና ሌሎች ሁለት ደግሞ ተገልጠው የማናያቸው ውጤቶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
9. የሰማይ አምላክ ስለሚመሰርተው የመንግስት ዓይነት በቁ44 ላይ ምን ማየት እንችላለን? መንግስቱንስ የሚመሰርተው መቼ ነው? የማይጠፉና የማይገረሰሱ የሚመስሉ ሁሉ አንድ ቀን መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን ይታይሃል? ጌታችን መንግስቱ መንግስታትን ሁሉ አፈራርሶ ልትመሰረት ቀኑ ቀርቧል፡፡

# ጥናት ስድስት ዳን 3፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- ለሰዎች መልካም ነገር ስናደርግ ነገ ለእኛ መልሰው ያደርጉልናል በሚለው ስሜት ተነስተን ሳይሆን ለእኛ በነነትን ካሳየን ከክርስቶስ የተነሳ መልካምን ማድረግ ከእኛ ከሁላችን እንደሚጠበቅ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ የሚባሉት አንዳንድ አይሁድ ትዕዛዝህን አይቀበሉም፣ አማልክትህን አያገለግሉም፣ አንተም ላቆምከው የወርቅ ምስል አይሰግዱም፡፡›› ዳን 3፡12

1. ዳን 3፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ናቡከደነጾር ያቆመው ምስል መጠኑ ምን እንደሚያህል ተናገር፡፡ለዚህ ምስል ምረቃ እንዲመጡ የተጠሩት ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ ዘርዝረህ ተናገር፡፡
2. እነ ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ ወደዚህ ምረቃ እንዴት ሊጠሩ ቻሉ? በቁ4 ላይ የታወጀው አዋጅ ምን የሚል ነበረ? እነዚህ ሶስት አይሁዳዊያን ምስል ለመመረቅ አንመጣም ሳይሉ የንጉስን ትዕዛዝ ለማክበር መወሰናቸው ምን ያስተምረናል?
3. በቁ2 መሰረት ሹማምንቱ የተጠሩት ለስግደት ነበረ ወይ? ካልሆነስ ሰምን ነበረ የተጠሩት? ለምርቃት ጠርቶ ስግደት ሲጠይቅ ይህ አስቀድሞ ያሰበው ነገር ወይስ በኋላ የመጣለት ሃሳብ ይመስልሃል? አንተስ እንደነሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ያልጠበከው ነገር ቢያፋጥጥህ በእምነትህ ጸንተህ ለመቆም ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
4. ለዚህ ምስል በማይሰግደው ሰው ላይ የሚወሰደው እርምጃ በቁ4-6 ውስጥ ምን ተብሎ ነው የተነገረው? የንጉሱ አዋጅ ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚነት አገኝቷል ማለት የምንችለው ለምንድነው? ለምስሉ ተደፍተው እንደሰገዱ ቁ7 የጠቀሳቸው እነማን በማለት ነው?
5. በቁ8-12 ላይ እነሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ የተከሰሱባቸው ሶስት ክሶች ምን ምንድናቸው? ክሱን የቀረበው ከማን ነው? ክሶቹ ትክክል ናቸው ብለህ ታምናለህ ወይ? አንተ በዚህ ጉባኤ ውስጥ ራስህን ብታገኝ በውሳኔህ በቁ4-6 ካሉት ጋራ ወይስ በቁ8-12 ካሉት ጋራ ትቆማለህ?
6. ንጉሱ በቁ13-14 ላይ ስናይ ከሰዎቹ ክስ የትኛውን እንደጣለው ነው የምንመለከተው? ቁ15 ላይ ‹‹…ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማን ነው?›› ይህ ጥያቄ ለምንድነው በ2፡47 ላይ ከተናገረው ሃሳብ ጋራ የሚቃረነው?
7. በቁ17 ላይ ጓደኞቹ ለንጉሱ የመለሱት መልስ እምነት የጎደለው ነው በሚለው ሃሳብ ትስማማለህ? ለምን? ዕብ 11፡33-34 ከዚህ አንጻር ምን ያስተምረናል? ‹‹ባያድነንም እንኳ›› የሚለው አነጋገር በዚህ ዘመን ስላለው ተቀባይነት ወይም ተቀባይነት ማጣት ተወያዩበት፡፡
8. ዳንኤልና ጓደኞቹ በዳን 2፡18 እና 24 ላይ ጠቢባኑን አስመልክቶ ያደረጉት ምን ነገር ትመለከታለህ? በዳን 3፡12 ላይ እነዚሁ የባቢሎን ጠቢባን በሶስቱ እብራውያን ላይ ሲያደርጉ የምትመለከተው ሁኔታ ምንድነው? አንተስ ለሰዎች መልካም ነገርን ስታደግ ከእነርሱ የምትጠብቀው ምን ነገር አለህ? በነነትን ለሰዎች ስናደርግ ነገ ለእኔ በነነትን ይመልሱልኛል በሚል አስተሳሰብ ሳይሆን ለሰዎቹ ካለን ፍቅርና ለእግዚአብሄር ትዕዛዝ ካለን አክብሮት ሊሆን ይገባል፡፡

# ጥናት ሰባት ዳን 3፡19-30

የጥናት ዓላማ፡- ልክ በሮሜ 8፡28 ላይ እንደምናነበው፤ ጠላታችን እኛን ለማጥፋት ያዘጋጀውን ወጥመድ ገልብጦ ለራሱ ለክብርና ለእኛም በጎ አድርጎ ሊጠቀምበት የሚችል አምላክ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና…ከዚያም ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብድናጎን በባቢሎን አውራጃ ላይ ሾማቸው፡፡›› ዳን 3፡29-30

1. ዳን 3፡19-30 በአንድነት ይነበብ፡፡ የንጉስ ናቡከደነጾርን ስሜት ሊገልጹ የሚችሉትን ሃሳቦች ከቁ19-20 ባሉት ውስጥ በማውጣት ተናገር፡፡ አንዳንዴ በንዴት ስሜት የማይሰጡ ነገሮች ይደረጋሉ፤ ንጉሱ በቁጣ ከወሰዳቸው እርምጃዎች ውስጥ ስሜት የማይሰጥ የሚመስልህ የትኛው ነው? ለምን? እኛም ብንሆን በቁጣ መንፈስ ተሞልተን እያለን የምንወስዳቸው እርምጃዎች እንደ ንጉሱ የተሳሳቱ ሊሆኑ ስለሚችሉ መጠንቀቅ ይጠይቃል፡፡
2. ቁ20-23 እነዚህ ሶስት አይሁዶች ወደ እሳቱ ስለገቡበት ሁኔታ የተነገሩን ነገሮች ምን ምንድናቸው? የእሳቱን ሃይለኛነት ሊያረጋግጥልን የሚያስችለንውና የሃይለኛነቱ መመዘኛ ሊሆነን የሚችለው የትኛው ሃሳብ ነው ትላለህ?
3. ቁ24-26 ላይ ‹‹ናቡከደነጾር በአድናቆት›› ሲል ንጉሱ የተደነቀው በምንድነው? ዳን 3፡25ትንና ሐዋርያት ሥራ 7፡59-60 በነዚህ ሶስት ሰዎችና በእስጢፋኖስ ሁኔታ ከእግዚአብሄር አሰራር ምን ትማራለህ?
4. በቁ26 ላይ ንጉሱ ለእነዚህ ሶስት ጓደኛሞች የሰጣቸው መጠሪያ ምን ነበረ? በዚህ ቁጥርና በቁ19 በምናየው የናቡከጾር ስሜት መሃል ምን ልዩነት ትመለከታለህ?
5. በቁ26-27 ላይ የእነ ሲድራቅን ከእሳት ውስጥ ሳይጎዱ መውጣት ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ሰዎች ሊመሰክሩ የሚችሏቸው እውነቶች ምን ምንድናቸው?
6. እንደ ናቡከደነጾር አነጋገር እነዚህ ሶስት ሰዎች የንጉሱን ትዕዛዝ መጣስ የቻሉት በምን ምክንያት ነበረ? ህይወታቸውን አሳልፈው መስጠት ድረስ ያደረሳቸው ነገርስ ምን ነበረ? የአንተ ልብስ ህይወትህን እስከምትሰጥ ድረስ የቆረጠ ነው ወይ?
7. እነዚህ ሶስት አይሁድ ወጣቶች በህይወታቸው በመቁረጣቸው ምክንያት አምላካቸው ባደረገው ተአምር የተነሳ ቁ29 ላይ ንጉሱ የደረሰበት የግል ውሳኔው ምን ነበረ? በዚህ ምንባብ ውስጥ የሶስቱ ጓደኛሞች መጨረሻቸው ምን ሆኖ ነው የምናየው? ቁ19 ላይ ንጉሱ የተናገረውን ሰምቶ ቁ30 ይመጣል ብሎ ማሰብ ምን ያህል ያስቸግር እንደሆነ ተወያዩበት፡፡
8. ይህ ሁኔታ ባይፈጠር የባቢሎን ንጉስና ሹማምንቱ የእግዚአብሄርን ተአምርና ድንቅ እንዲመለከቱ እነዚህ ሶስት ጓደኛሞች ምን ማድረግ ይችሉ ነበረ ትላለህ? በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሄር በሮሜ 8፡28 የተነገረንን እውነት በስራ ላይ ሲያውል ያየህበትን መንገድ አስረዳ፡፡ ጌታ ለክፉ የመጣብህን ለእርሱ ክብርና ለአንተም በረከት አድርጎ መለወጥ እንደሚችል አትዘንጋ፡፡

# ጥናት ስምንት ዳን 4፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- መንግሥታትን ሁሉ የሚገዛ፣ መንግሥትንም ለወደደው የሚሰጥ፣ በሰው የተናቁትንም መሾም የሚችል ታላቅ አምላክ በሰማይ ስላለ ሳንኩራራ በፊቱ በትህትና መመላለስ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ልዑል በሰዎች መንግሥታት ሁሉ ላይ እንደሚገዛና እነዚህንም መንግስታት ለወደደው እንደሚሰጥ፣ ከሰዎችም የተናቁትን በላያቸው እንደሚሾም፣ ህያዋን ሁሉ ያውቁ ዘንድ ነው፡፡›› ዳን 4፡17

1. ዳን 4፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ ንጉሱ ሃሳቡን ማስተላለፍ የፈለገው ለማን ነበረ? ቁ2-3ትን ስታነብ የመልዕክቱ ዋነኛ ሃሳብ ምን ነበረ ትላለህ?
2. ንጉሱ መልዕክቱን ስለ ሚያስተላልፍበት መንፈስ ከእነዚህ ቁጥሮች ምን መረዳት እንችላለን? ይህ ሰው በተለይም በቁ3 ላይ ስለ እግዚአብሄር የተናገራቸው አራት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
3. ስለ ንጉሱ ናቡከደነጾር አኗኗር ከቁ4-5 ባሉት ቁጥሮች ምን እንመለከታለን? በዚህ ዓይነት የተደላደለ ኑሮ ውስጥ ሆኖ የገጠመው ነገር ምን ነበረ? ይህስ የገጠመው ነገር በህይወቱ ያስከተለው ነገር ምንድነው? ከዚህ ሁኔታ ምን ለራስህ ምን መማር ትችላለህ?
4. በዳን 2፡1-6 ላይ ጠቢባኑም ሆኑ ዳንኤል ከተጠየቁት ጥያቄ ይልቅ በ4፡4-8 ከሚገኘው ጥያቄ ቀለል ያለ ነው ማለት የሚቻለው ለምንድነው ትላለህ?
5. በቁ10-12 ላይ ንጉሱ ያየው አንድ ነገር ምን ነበረ? ንጉሱ በተመለከተው ነገር ውስጥ የተካተቱት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ግለጽ፡፡
6. ቁ13-16 ላይ የሚነበበው መልዕክት ለናቡከደነጾር የተላለፈው በማን በኩል ነበረ? የመልዕክቱ አጠቃላይ ሃሳብ ምን እንደነበረ በአጭሩ ተናገር፡፡
7. ይህ ሁሉ ነገር በዛፉ ላይ ሊመጣ ስላለበት ምክንያት መልዕክተኛው በቁ17 ላይ የሚናገን ነገር ምንድነው? አንተስ ከእግዚአብሄር የተቀበልከውን ሥልጣንም ሆነ መንፈሳዊ ሥጦታ እንደራስህ አድርገህ ትመካበታለህ ወይ?
8. ቁ6-7 እና ቁ18ትን ስናነብ፤ ናቡከደነጾር አስቀድሞ ለጥያቄው መልስን ለማግኘት የሞከረው ከየት ነበረ? ለጥያቄው መልስ የመጨረሻውን ሥፍራ የሰጠው ለማን ነበረ? አንተስ ለህይወትህ ጥያቄ በመጀመሪያ ወደማን ትሄዳለህ? የጥያቄ መልስ ሁሉና የእንቆቅልሽ ፍቺ በእርሱ እጅ ወደ ሆነው ጌታ ከሁሉ አስቀድመህ መሄድ ከብዙ ሃዘንና ክስረት ያድንሃል፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ዳን 4፡19-37

የጥናት ዓላማ፡- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ የእግዚአብሄርን ፍቅርና መልካምነት ከመጠራጠር ይልቅ፤ የልባችንን ክፉነት አምነን በመቀበል፤ እርሱ በሚያደርገው ሁሉ ትክክል፣ መንገዶቹም ሁሉ ጽድቅ እንደሆኑ በማመን ለስሙ ክብር መስጠትና እርሱን ከፍ ከፍ ማድረግ የተሻለ እንደሆነ ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጊዜው ከተፈጸመ በኋላ፣ እኔ ናቡከደነጾር አይኖቼን ወደ ሰማይ አነሳሁ፤… የሰማይ አምላክ የሚያደርገው ሁሉ ትክክል፣ መንገዶቹም ሁሉ ጽድቅ ስለሆኑ አሁንም እኔ ናቡከደነጾር እርሱን አወድሰዋለሁ፣ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፣ አከብረዋለሁም›› ዳን 4:34-37

1. ዳን 4፡19-37 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-18 ናቡከደነጾር ስላየው ዛፍ ዳንኤል እንዲተረጉም በቁ19 ላይ በተጠየቀ ጊዜ ስለተሰማው ስሜት ክፍሉ ምን ይናገራል? ዳንኤል በዚህ ሥፍራ የዚህ አይነት ስሜት የተሰማው ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
2. ቁ20-23 ሲነበብ ንጉስ ናቡከደነጾር በህልሙ ውስጥ የተመሰለው በምን ነበረ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለዛፉ የተሰጡት መግለጫ ቃላት ምን ነበሩ? ስለዚህ ዛፍ ቅዱሱ መልዕክተኛ የተናገራቸውስ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ቁ24-25 በናቡከደነጾር ላይ አዋጅ እንደወጣ እናነባለን፡፡ በዳንኤል ፍቺ መሰረት አዋጁን ያወጣው ማን ነው? ዳን 2፡37 እንደሚነግረን የነገስታት ንጉስ በሆነው በናቡከደነጾር ላይ እግዚአብሄር አዋጅ ማወጅ መቻሉ ምን ያስተምርሃል?
4. በቁ15 ላይ የተነገረውን የአዋጅ ክፍልና ቁ26-27ን በአንድነት ስናነብ፤ እግዚአብሄር ለዚህ ሰው ያለውን ምህረትና ቸርነቱን የሚያረጋግጥልን እንዴት ነው? ዳንኤል ከትንቢቱ ፍቺ ጋራ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለንጉሱ የሚሰጣቸው አራት አይነት ምክሮች ምን ምንድናቸው? አምላካችን በቅጣት ውስጥ እንኳን ምህረትና ርህራሄን ጨምሮ የሚያስኬድ ደግ አምላክ ነው፡፡
5. ቁ17፣ 25ትና 32ትን ስታነብ እግዚአብሄር ንጉሱን ናቡከደነጾርን ሊያስተምር ቆርጦ የተነሳቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው ትላለህ? ቁ28-30 ላይ ያለው ሃሳብ እግዚአብሄር ሊያስተምረው ከወሰነው ነገር ጋራ የሚቃረነው በምን መንገድ ነው?
6. ቁ28ትና ቁ33 ስናነብ እግዚአብሄር ከተናገረው ምን ያህሉ ነው በናቡከደነጾር ላይ የደረሰበት? ማር 13፡31 የሚናገረውን ይህ ክፍል እንዴት ያጠናክረዋል?
7. በቁ28-30 ያየነው ናቡከደነጾር በቁ34-35 ስትመለከት ምን ልዩነት ትመለከታለህ? በቁ37 ላይ ‹‹በትዕቢት የሚመላለሱትን ማዋረድ ይችላል›› የሚለው አነጋገሩ ከመጽሃፍ ቅዱስ የሚያስታውስህ የትኛውን ጥቅስ ነው? እግዚአብሄር ከትዕቢት በላይ የሚጠላው ሃጥያት አለ ብለህ ታምናለህ ወይ? ተወያዩበት፡፡
8. ቁ34 ላይ የውርደት ጊዜው ሲፈጸም ንጉስ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ቁ37ትን ስናይ ንጉሱን ለምስጋና ያበቁት ስለእግዚአብሄር ባህይ የተማራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማለፍህ ወደ እግዚአብሄር ያስጠጋሃል ወይስ እልከኛ ያደርግሃል? በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማለፍህ ዓይንህን ወደሰማይ የሚያስነሳህና የአምላክን ትክክለኛነት የሚያሳይህ እንጂ በእልከኝነት የእርሱን በጎነት የምታቃልልበት እንዳይሆን ልትጠነቀቅ ይገባሃል፡፡

# ጥናት አስር ዳን 5፡1-17

የጥናት ዓላማ፡- ዳንኤል በእውቀት፣ በማስተዋልና በብዙ ልዩ ልዩ ችሎታዎች ከመባረኩም አልፎ መልካም መንፈስ የነበረው ሰው እንደነበረ እንደተመሰከረለት ሁሉ፤ እኛም እግዚአብሄር በውስጣችን ካኖራቸው ማናቸውም ስጦታዎች በተጨማሪ ሰዎች በውስጣችን መልካም መንፈስን ማየት እንዲችሉ ለማበረታታት፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ንጉሱ ብልጣሶር ብሎ የጠራው ይህ ዳንኤል መልካም መንፈስ፣ እውቀትና ማስተዋል ያለው ሆኖ ተገኘ›› ዳን 5፡12

1. ዳንኤል 5፡1-17 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-4 ሲካሄድ የሚታየውን ሃሳብ አጠር በማድረግ ተናገር፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው አንድ ቃል ምን የሚል ነው? የዚህ ቃል መደጋገም በዚህ ግብዣ ውስጥ ስለነበረው መንፈስ ምን ሊነግረን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
2. በዚህ ቦታ የሚጠጣባቸው እቃዎች ባለቤት ማን ነበረ? በእቃዎቹ እየጠጡ ግን የሚያመሰግኑት ማንን ነበረ? ይህ ንጉስ ቤልሻዛር የእግዚአብሄርን ቤት እቃዎች መጠቀም ያስፈለገው በቤተ መንግሥቱ ሌላ መጠጫ ስለሌለ ነው ወይስ ለምን ይመስልሃል?
3. በቁ5 ላይ ስናነብ ንጉሱ በግድግዳ ላይ የጻፉትን ጣቶች ባየ ጊዜ በንጉሱ ላይ የተከሰቱት ስሜቶች ምን ምንድናቸው? ቤልሻዛር ቀጥሎ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ጽህፈቱን አንብቦ ትርጉሙን ለሚያስታውቀው ሰው ሊያደርግ ቃል የገባቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡
4. በቁ8-9 ላይ በጠቢባኑ ጽሁፉን ለማንበብም ሆነ ለመተርጎም አለመቻላቸው የተፈጠረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበረ? በቁ10-12 ላይ በአጭሩ የንግስቲቱ ምክር ለንጉሱ ምን ነበረ?
5. በቁ14ና በቁ16 ላይ ንጉሱ ስለዳንኤል ሰምቻለሁ የሚላቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? በቁ11 ላይ ንግስቲቱ ዳንኤል ስለሞላበት መንፈስና፤ በቁ14 ላይ ንጉሱ ስለዚሁ ሁኔታ በሚናገርበት መሃል ምን ልዩነት ትመለከታለህ? አንተስ የቅዱሱ የእግዚአብሄር መንፈስ በውስጥህ እንደሚኖር ሰዎች ምን ያህል ማየት ይችላሉ?
6. በቁ16 ላይ ‹‹አንተ ግን›› የሚለው አነጋገር ዳንኤልን ከማን ለመለየት የተነገረ አነጋገር ነው? በዚሁ ቁጥር ላይ ለዳንኤል ጽሁፉን ለማንበብና ለመተርጎሙ ሊሰጠው ስላለው ክፍያ ምን ትመለከታለህ?
7. ለማንበቡና ለመተርጎሙ ከንጉሱ በቁ16 ላይ ለቀረበለት የስጦታ አይነት የዳንኤል ምላሽ ምን ነበረ? የበ4፡19 ላይ ለናቡከደነጾር ያሳየው ሁኔታና በዚህ በ5፡17 ላይ ለዚህ ሰው ካሳየው ልዩ ሆኖ የሚሰማህ ነገር አለወይ? ካለስ ምንድነው? አንተስ በነጻ የተቀበልከውን በነጻ ለመስጠት ምን ያህል የተከፈተ ልብ አለህ?
8. ቁ12ትን መለስ ብለን ስናይ በዳንኤል ላይ የምናያቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ዳንኤል ይህ ሁሉ ችሎታና እውቀት እያለው፤ ከዝርዝሮቹ መሃል በአንደኛነት የተጠቀሰው ምን ነበረ? ሰዎች በአንተ ውስጥ ከስጦታዎችህ አልፈው መልካም መንፈስ እንዳለህ ማየት ይችላሉ ወይ? ስጦታዎች በበለጠ ፍሬያማ ሊሆኑ የሚችሉት በመልካም መንፈስ ስናገለግልባቸው ስለሆነ መልካምና የቀና መንፈስ ይኑርህ፡፡

# ጥናት አስራ አንድ ዳን 5፡18-31

የጥናት ዓላማ፡- በሰዎች ህይወት ሲያልፍ የምናየው ማናቸውም ነገር ለእኛ ትምህርት ሆኖልን ከውድቀታቸው እንድንማርና እንድንታረም እንጂ የእኛን ከእነርሱ መሻል የምናረጋግጥበትና ለትደዕቢት የሚዳርገን እንዳይሆን መጠንቀቅ እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ቤልሻዛር ሆይ፤ አንተ ልጁ ሆነህ ይህንን ሁሉ ብታውቅም፣ ራስህን ዝቅ አላደረክም፤ ይልቁንም በሰማይ አምላክ ላይ በመታበይ ራስህን ከፍ ከፍ አደረግህ›› ዳን 5፡22-23

1. ዳንኤል 5፡18-31 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ18-19 አነጋገር የቤልሻዛር አባት ከልዑል አምላክ የተሰጡት ነገሮች ምን ምን ነበሩ? ሰዎች ሁሉ ናቡከደነጾርን የተንቀጠቀጡለትና የፈሩበት ምክንያት ለምን ነበረ?
2. በቁጥር 19 ላይ ብቻ ቢያንስ አራት ጊዜ ያህል የተጠቀሰ አንድ ቃል ምን የሚለው ቃል ነው? ይህንን ሁሉ ማድረግ መቻሉ በንጉሱ ልብ ውስጥ ያመጣው ምን ነበረ? አንተስ እግዚአብሄር እንድትመራም ሆነ እንድታስተዳድር የሰጠህን ሥልጣን ወይም ሃላፊነት በቤተሰብ፣ በበልጆች፣ ቤተ ክርስትያን… ወዘተ ምን ያህል በጥንቃቄና በትህትና ትጠቀምበታለህ?
3. ቁ20-21ድን ስናነብ የቤልሻዛር አባት ከእግዚአብሄር የተቀበለው ሥልጣን መሆኑን ሲዘነጋና በትዕቢት ሲሞላ የደረሰበት ሁኔታ ምንድነው? የዚህ ንጉስ በውርደትና በውድቀት መቆየት ለምን ያህል ጊዜ ነበረ?
4. በቁ18-24 ዳንኤል ጽሁፉን አስመልክቶ ምንም የተናገረው ነገር አናይም፡፡ ለነዚህ ቁጥሮች የራስህ የሆነ ርዕስ ስጥ ብትባል ምን ርዕስ ትሰጣለህ?
5. በዳን 5፡4 ላይ ለተዘረዘሩት አማልክቶቻቸው ዳንኤል 5፡23-24 ላይ ሲሰጣቸው የምንመለከተው መግለጫዎች ምንድናቸው? ይህ ጽሁፍ እንዲጻፍ ካበቁት መሃል ቤልሻዛር እነዚህን አማልክቶቹን ከማመስገን ሌላ ትልቅ ጥፋት ያደረገው ምን ነበረ? አንተስ ለመሆኑ እግዚአብሄር ህይወትህንም ሆነ አረማመድህን በእጁ እንደያዘ ምን ያህል ተገንዝበሃል?
6. ቁ25-30 ዳንኤል የተደረገለት ነገር ምንድነው? ዳንኤል ስጦታን ለማግኘት ብሎ እንዳልተረጎመ መረዳት የምንችለው እንዴት ነው? አንተስ ከእግዚአብሄር የተቀበልከውን ስጦታ ማትረፊያ በማድረግ የተጠቀምክበት ጊዜ ይኖር ይሆን?
7. በሁለቱ ነገስታት ማለትም በናቡከደነጾርና በልጁ በቤልሻዛር ላይ እግዚአብሄር ባመጣው ፍርድ መሃል የምታያቸውን ልዩነቶች በሙሉ ተናገር፡፡
8. ቁ22-23 አነጋገር የዚህ ሰው ሃጥያት ከብዶ የተገኘበት ምክንያት ለምንድነው? አንተስ በሰዎች ህይወት ከምታየው ለራስህ ምን ያህል ትምህርት ትቀስማለህ? ከሰዎች ውድቀት በመማር ህይወትህን ማረም እንጂ የትዕቢትን ነገር ልብህ ውስጥ እንዳታስገባ ልትጠነቀቅ ይገባሃል፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት ዳን 6፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር በማናቸውም ዓይነት ስፍራ ቢያስቀምጠን፤ ታማኞች፣ ጠንቃቆችና ግድ የለሽነት የማይታይብን ዓይነት ሰዎች ሆነን በመመላለስ ለጠላታችን የክስ ምክንያት ማሳጣት እንደሚኖርብን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ዳንኤል ታማኝ፣ ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለበት ነበረ፤ በእርሱም ላይ ስህተት ሊያገኙ አልቻሉም፡፡›› ዳን 6፡4

1. ዳን 6፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1-2 ላይ ንጉስ ዳርዮስ በባቢሎን ላይ እንደነገሰ የወሰዳቸው የመጀመሪያ እርምጃዎች ምን ምን እንደነበሩ ተናገር፡፡ ለምንድነው ንጉሱ በዚህ ዓይነት መንግስቱን ማዋቀር የፈለገው? ይህ ‹‹ጉዳት እንዳይደርስበት›› የሚለው ምን ማለቱ ይመስልሃል? ከዚህ አንጻር አሰሪህ (ቀጣሪህ) ጉዳት እንዳይደርስበት በአንተ በኩል ምን የምታደርገው አስተዋጽዖ አለ?
2. በቁ3 ላይ ንጉሱ ዳንኤልን በመላ ግዛቱ ላይ ሊሾመው የፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ም ነበረ? በዳርዮስ መንግስት መዋቅር ውስጥ ከንጉሱ ጀምረህ ወደታች እስከምታውቀው ድረስ በተዋረድ ለመናገር ሞክር፡፡
3. በቁ4-5 መሰረት እነዚህ ዳንኤልን ሊከሱ የተነሱት ሰዎች በመጀመሪያ ለመክሰስ የተነሱት በምን ዙሪያ ነበረ? እነዚህ ሰዎች ዳንኤልን ለማግኘት እንደሚችሉ እርግጠኛ ሊሆኑ የሚችሉበት ስንት መንገዶች ነው ማየት የቻሉት? መንገዱ ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
4. በቁ6-9 ላይ የተካሄደውን ነገር በአጭር አረፍተነገር ተናገር፡፡ ይህንን ክፍል ሰታነብ የዳንኤል ከሳሾች ስለዳንኤል መንፈሳዊ ህይወት የተረዱት አንድ እውነት ምንድነው ትላለህ? ሰዎች በአንተ መንፈሳዊ ህይወት ውስጥ እንደዚህ በእርግጠኛነት መናገር የሚችሉት መልካም ነገር ምንድነው ትላለህ?
5. ቁ1-9ን በመመርኮዝ የበላይ አስተዳዳሪዎቹንና መሳፍንቱን ባህርይ ሊገልጽ ይችላል ብለህ የምታስበው አንድ ቃል ምንድነው? ንጉስ ዳርዮስ በወሰደው ውሳኔና እርምጃ ውስጥ ምን ስህተት ታያለህ? ከባለስልጣኖቹ ባህርይና ከንጉሱ ከወሰደው ውሳኔ መማር የምንችላቸው ነገሮች ተናገር?
6. በቁ10 ላይ ንጉሱ ያወጣው አዋጅ ዳንኤል ከእግዚአብሄር ጋራ ባለው ግንኙነት ላይ ያመጣው ምን ለውጥ ታያለህ? ‹‹መስኮቶቹ በኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው›› የሚለው አነጋገር የዳንኤልን ቆራጥነት የበለጠ ጉልህ አድርጎ የሚያሳየን በምን መንገድ ነው? ዳንኤል ይህንን ሲያደርግ ሮሜ 13፡1-2ትን አልተላለፈም ወይ? ለምን?
7. ቁ13-15 ተላላፊው ሰው ዳንኤል መሆኑን ሲያውቅ ንጉሱ የተሰማው ስሜት ምን ነበረ? የወሰደው እርምጃስ ምን ነበረ? ለምን ይመስልሃል ንጉሱ የዚህ ዓይነት ስሜት የተሰማው? የአንተስ አለቃ ተንኮል ቢሸረብብህ የሚያዝንበትና ሊያድንህ የሚፈልግበት ምንክያትን በህይወትህ አሳይተኸዋል ወይ?
8. ዛሬ ባነበብነው ክፍል ዳንኤልን ከሳሾቹን ምክንያት ማሳጣት የቻለባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው ብለህ ብትጠየቅ ምን ትላለህ? አንተስ ከሳሾችህ ምክንያት ቢፈልጉብህ የምትከሰሰው በምን ይሆን? በታማኝነት፣ በጥንቃቄና በሥራህ እንከን የሌለብህ ሆነህ በመገኘት ለጠላት የክስ በትን ዝጋበት፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት ዳን 6፡16-28

የጥናት ዓላማ፡- ዳንኤል የእግዚአብሄርን ህግ ለመታዘዝ ቅድሚያ ሲሰጥ እርሱ ደግሞ በኑሮው መሳካትን እንደሰጠው ሁሉ፤ እኛም አስቀድመን የእግዚአብሄርን ጽድቅና መንግስቱን በመሻት ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር ሊሆን እንደሚገባ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ስለዚህ ዳንኤል በዳርዮስ ዘመነ መንግስትና በፋርሳዊው በቂሮስ ዘመነ መንግስት ሁሉ ኑሮው ተሳካለት፡፡›› ዳን 6፡28

1. ዳን 6፡16-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ16 ላይ ስንመለከት ከዳንኤል ከሳሾችና ከዳንኤል አሸናፊ የሚመስለው ማነው? አስረዳ፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ ንጉሱ ዳንኤልን የተሰናበተው ምን በማለት ነበረ?
2. ቁ17-18 በዳንኤል ላይ በተደረገውና በማቴ 27፡60-66 በኢየሱስ ሬሳ ላይ በተደረገው ነገር የሚመሳሰሉበትን ሁለት ነገሮች ተናገር፡፡ በተለይ ቁ18 በዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ መጣል ንጉሱ ስለተሰማው ስሜት ምን ይነግረናል?
3. ቁ19-20 በማንበብ፤ ንጉሱ ያቺ ሌሊት እንደረዘመችበት የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው? ናቡከደነጾር በእግዚአብሄር ማዳን ሙሉ እምነት ነበረው ብለን በእርግጠኛነት መናገር ባንችልም፤ የእምነት ጭላንጭል የምናይበት ከየትኛው ድርጊቱ ነው?
4. ቁ20 ላይ ‹‹ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ›› ሲል ምን ትረዳለህ? አንተስ ጌታህን የምታመልከው ሁልጊዜ ማለትም፣ በማግኘትም፣ በማጣት፣ በጤንነት በበሽታ፣ በደስታ በሃዘን…ወዘተ፡፡ ሁልጊዜ አምላኩን እንደሚያመልክ ለዳንኤል ንጉስ እንደመሰከረለት፤ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ስለኛ ይህንን መናገር ይችላሉ ወይ?
5. በቁ21-23 አነጋገር ዳንኤል መልካም የሆነ የህይወት ምስክርነትን የነበረው በማን ዘንድ ነው?
6. ንጉሱን በቁ18 ላይና በቁ23 ላይ ስትመለከተው የምትገነዘበው አንድ ልዩነት ምንድነው? ለዚህ ስሜቱ መለወጥ ምክንያት የሆነው ነገርስ ምን ነበረ? ለዳንኤል አለመሞት ንጉሱ ይህንን ያህል ትኩረት የሰጠበት ምክንያት የሚመስሏችሁን ምክንያቶች ተወያዩባቸው፡፡
7. ቁ24 ላይ የዳንኤል ከሳሾች እድላቸው ምን ሆነ? በነበሩ ውስጥ ያልነበሩ ነገር ግን ወደ አንበሳው ጉድጓድ የተጣሉት እነማንን ታያለህ? የአንተ ሃጥያት አንተን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብህንና ሌሎችን ጨምሮ የማጥፋት ችሎታ እንዳለው ምን ያህል ገብቶሃል?
8. ቁ25-28 ዳንኤል ያሳለፈው ሁኔታ ለእግዚአብሄር ስም ያመጣው ነገር ምንድነው? ዳንኤል ለሹመቱ፣ ወይም ለኑሮው መሳካት፣ ለእድገቱ ሲያደርግ የምናየው ምን ነገር አለ? ቁ28 ስለዳንኤል ኑሮ የሚነግረን ነገር ምንድነው? ከዚህ ሰው ህይወትና ማቴ 6፡33 ትን በማየት ለህይወትህ ምን ትማራለህ? ለእግዚአብሄር በመታዘዝ በጽድቅ ለመኖር ቆርጠህ መኖር ብትጀምር የአንተን ኑሮ ማሳካት እግዚአብሄር ሃላፊነቱን እንደሚወስድ ልትረዳ ያስፈልግሃል፡፡

# ጥናት አስራ አራት ዳን 7፡1-28

የጥናት ዓላማ፡- ዳንኤል የሌሎችን ህልምና ራዕይ መፍታት ችሎ የራሱን ህልም ግን መረዳት እንዳልቻለ፤ አንዳንድ ጊዜ እኛም የሌሎችን እንቆቅልሽና ችግር ለመፍታት የምንችልበትን ጸጋ ይሰጠንና፤ የእኛን ደግሞ ለመፍታት ሌሎች እንዲያስፈልጉን እግዚአብሄር የሚያደርግባቸው ጊዜያት ሊኖሩ እንደሚችሉ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እኔ ዳንኤል በመንፈሴ ታወከሁ፤ ያየሁትም ራዕይ እጅግ አስጨነቀኝ፡፡ በዚያ ከቆሙት ወደ አንዱ ቀርቤ፤ የዚህ ሁሉ እውነተኛ ትርጉም ምን እንደሆነ ጠየቅሁት፡፡›› ዳን 7፡15-16

1. ዳን 7፡1-28 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ላይ ዳንኤልን የምናገኝበት ሁኔታ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከምናየው የሚለየው በምን መንገድ ነው? ዳንኤል በህልሙ የተመለከተው ነገር ምን እንደነበረ ተናገር፡፡ ስለ አራቱ አራዊት ዳንኤል የነገረንን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ጥቀስ፡፡
2. የመጀመሪያው እንስሳ አንበሳ (ቁ4)፣ ሁለተኛው ድብ (ቁ5)፣ ሶስተኛው ነብር (ቁ6) ነበሩ በሚለው አነጋገር ትስማማለህ ወይ ለምን? ለመጀመሪያዎቹ ሶስት እንስሶች ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ነገር ምንድነው?
3. ቁ7 ላይ የተመለከተውን አውሬ ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ይህንን አውሬ ከሌሎቹ ሶስት አውሬዎች የሚለየው ዋነኛ ነገር ምንድነው ትላለህ? በቁ9-10 ላይ ዳንኤል የተመለከተው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር፡፡
4. በቁ13-14 ‹‹የሰውን ልጅ የሚመስል›› የሚለው አነጋገር ስለማን መናገሩ ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሲከናወን የምንመለከተው ነገር ምንድነው? አንተስ እስከዚያን ቀን ድረስ ሳትጠብቅ ዛሬ ልታመልከው የተሰጠህን እድል ምን ያህል ትጠቀምበታለህ?
5. በቁ1-7 ያነበብናቸው አራዊት ሁሉ ቁ17-20 ላይ የሚያመለክቱት ምንድነው ይለናል? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የመንግሥታቱ ሁሉ መጨረሻ ምን እንደሆነ ነው የምናነበው? ዳንኤል ከህልሙ መሃል በተለይ ለማወቅ አጥብቆ የፈለጋቸው ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
6. ቁ21-22 ላይ ቅዱሳን ምን ሲሆኑ ታያለህ? ይህ በቅዱሳን ላይ የሆነው ነገር ጊዜያዊ እንደሆነ የምናውቀው እንዴት ነው? አንተስ ለጊዜው ጠላትህ ያሸነፈህ የመሰለህ ነገር በህይወትህ አለ ወይ? ለቅዱሳን እግዚአብሄር እንደሚመጣላቸው ልታስብ ይገባሃል፡፡
7. በቁ23-25 ባለው ክፍል ሲሆን የምታየውን በራስህ ቋንቋ ተናገር፡፡ ቁ26-28 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ምን እንደሆነ ተናገር፡፡ ‹‹የነገሩ ፍጻሜ ይህ ነው›› ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. ቁ15-16ትን መለስ ብለን ስናይ፤ ዳንኤል ስላየው ህልም የተሰማው ስሜት ምን ነበረ? ከዚህ በፊት ሰዎች ዳንኤል ህልማቸውን እንዲፈታላቸው ሲጠይቁትና ሲፈታላቸው አይተናል፤ በዚህ ክፍል በተለይ በቁ16 ላይ ዳንኤል ምን ሲያደርግ ነው የምናገኘው? የሌሎቹን ህልም ፈትቶ የራሱን ህልም ግን ሊፈታለት ሌላ ሰው ማስፈለጉ ምን ያስተምርሃል? ሌሎች እንደሚያስፈልጉህና አንተም ለሌሎች እንቆቅልሽ ፍቺ እንደምታስፈልግ አስተውል፡፡

# ጥናት አስራ አምስት ዳን 8፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ጠላቶች ለሆኑት እንኳን ለጊዜው የሚያደርጉት ሁሉ ሊሳካላቸውና ሊከናወንላቸው እንደሚችል፤ ደግሞም የነገሮች መሳካት ሁልጊዜ የእግዚአብሄር በረከት በእኛ ላይ አለ ማለት እንዳልሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹…ከአመጽ የተነሳም የቅዱሳን ሰራዊት ከዘወትሩ መሥዋዕት ጋራ ለእርሱ አልፎ ተሰጠ፤ የሚያደርገው ሁሉ ተከናወነለት፤ እውነትም ወደ ምድር ተጣለች፡፡›› ዳን 8፡12

1. ዳን 8፡1-27 በአንድነት ይነበብ፡፡ በምዕራፍ 7 ውስጥ ዳንኤል በተመለከተውና በዚህ ክፍል በተመለከተው ራዕይ መሃል የነበረው የጊዜ ርቀት ምን ያህል ነበረ? በመጀመሪያ ዳንኤል ያየው እንስሳ ምን ነበረ? በቁ1-4 ላይ ስለዚህ እንስሳ የተነገሩትን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡
2. በቁ5-8 ዳንኤል ምን በማድረግ ላይ እያለ ነው ሌላ እንስሳ የታየው? በዚህ ጊዜ ያየው እንስሳ ምን ነበረ? ስለ አመጣጡ አቅጣጫስ ምን እናነባለን?
3. በአውራ በጉና በአውራ ፍየሉ መሃል ስለተካሄደው ነገር ሁሉ ቁ6-8 የሚናገሩትን ዘርዝር፡፡ የፍየሉ ትልቁ ቀንዱ የተሰበረበት መቼ ነበረ? በትልቁ ቀንድ መሰበር ምክንያት የተፈጠረው ነገርስ ምን ነበረ?
4. በቁ9 ላይ የምናየው ምን ሲሆን ነው? ይህ አዲስ የወጣው ቀንድ በቁ10-14 ላይ የሚያደርጋቸው ነገሮች ከሌሎቹ ሁሉ ቀንዶች የሚለየው ምን ታያለህ? በቁ10-14 ላይ ያሉት ነገሮች ስለሚፈጸሙበት ጊዜ ክፍሉ ምን ይነግረናል?
5. በ15-17 ውስጥ ለዳንኤል የራዕዩን ትርጉም እንዲነግረው የተነገረው ለማን ነው? ዳንኤል እንዲያስተውል የተነገረው አንድ ነገር ምን ነበረ? ቁ17 19ኝና ቁ27ትን በማንበብ ራዕዩ ሊፈጸም ስላለበት ዘመን በእርግጠኛነት መናገር የምንችለው ነገር ምንድነው ትላለህ?
6. ቁ1-8 ሲነበብ አውራ በግ የተባለው በዚህ በቁ 19-22 ውስጥ ስናይ ትርጓሜው ምንድነው? ፍየሉስ ምንን የሚያመለክት እንደሆነ ነው ለዳንኤል የተነገረው? ስለ አራቱ ቀንዶችስ በ22 ላይ ምን ተነግሯል?
7. ከአራቱ ቀንዶች በመቀጠል ስለሚመጣው መንግሥት ቀ23-25 የሚናገራቸውን ሃሳቦች በሙሉ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ይህ ንጉስ የጥፋቱ ዓይነት እየከፋ መሄዱን የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? ቁ24 ላይ ‹‹…በገዛ ሃይሉ አይደለም፡፡›› ሲል ምን ትረዳለህ?
8. በቁ26-27 ላይ ዳንኤል ራዕዩንና ትርጉሙን ሳይጠራጠር እንዲቀበል የነገረው ነገር ምንድነው? የተመለከተው ራዕይ በዳንኤል ላይ ያስከተላቸው ቢያንስ አምስት ነገሮችን ተናገር፡፡ ‹‹…ተነስቼ ወደ ንጉሱ ሥራ ሄድሁ›› ከዚህ አይነት መንፈሳዊ ልምምድ በኋላ ወደሥራው መመለሱ ምን ያስተምርሃል?
9. ቁ11-12 እና ቁ24ትን ስናነብ ‹‹የሚያደርገው ሁሉ ተከናወነለት›› የሚል እናነባለን፡፡ በዚህ ሥፍራ የተከናወነለት ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው? ምንጊዜም የማደርገው ነገር ከተከናወነልኝ የማደግገው ነገር የጌታ የበረከቱ እጅ አለበት በሚለው አመለካከት ትስማማህ ወይ? ለምን? ክፉዎችና የጌታ ጠላቶችም ስለሚከናወንላቸው የነገሮች ክንውን የእርሱን በረከት እንደማያመለክት እወቅ፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት ዳን 9፡1-27

የጥናት ዓላማ፦ የተሰማራንበት ማንኛቸውም ዓይነት ሥራ ቢሆን የእለት እንጀራችንን የምንሰራበት ብቻ ሳይሆን፤ በዚያ ሥፍራ የእግዚአብሄር አምባሳደሮችና አገልጋዮች መሆናችንን በመገንዘብ በትህትናና በትጋት ማገልገል እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹አሁንም አምላካችን ሆይ የአገልጋይህን ጸሎትና ልመና ስማ።›› ዳን 9፡17

1. ዳን 9፡1-27 ያለው በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ዳንኤል ምን ሲያደርግ ነው የምንመለከተው? ምን ነበረ ዳንኤልን ወደ ጸሎት እንዲሄድ ያነሳሳው ነገር? ዳንኤል በጣም ብዙ ሃላፊነትና ሥራ ያለበት ሰው ሆኖ እያለ ቃሉን የማጥናት ልምድና የጸሎት ልምድ ማዳበሩ፤ ለጸሎትም ሆነ ለቃሉ ጊዜ የለኝም ለምንል ለእኛ ምን ትምህርት ይሰጠናል ብለህ ታምናለህ?
2. ቁ4-6ትን በማንበብ ዳንኤል በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄርን የሚገልጥባቸው መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። ይህ ክፍል የእስራኤልን ህዝብስ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው የሚገልጸው?
3. ዳንኤል የሚኖረው በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆኖ እያለና በምኞት የፈለገውን መብላት መጠጣት በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ እያለ፤ ለምንድነው በቁ7 ላይ ‹‹በዚህ ቀን በሃፍረት ተከበናል።›› በማለት የሚናገረው? ዛሬ በቤተ ክርስትያን ውስጥ የምታየው ውድቀትና ሃጥያት አንተንስ ምን ያህል ለንስሃ ጸሎት ያነሳሳሃል?
4. ቁ7-12 በማንበብ ዳንኤል በህዝቡና በኢየሩሳሌም ላይ ለደረሰው ነገር ሁሉ ጥፋተኛ አድርጎ የሚያየው ማንን ነው? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ዳንኤል ስለ እግዚአብሄር ባህርይ የሚናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በአንተስ ህይወት እነዚህን ሶስት ባህርዮች ምን ያህል ተለማምደሃቸዋል?
5. በቁ13-14 አነጋገር፤ ከእግዚአብሄር ምህረትን የሚፈልግ ሰው ማድረግ የሚገባው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ይህንኑ ክፍል ስናነብ እግዚአብሄር በኢየሩሳሌምና በህዝቡ ላይ የወሰደው እርምጃ የምን ማረጋገጫ ሆኖ ነው የቀረበው? አንተስ ከእግዚአብሄር ምህረትን ስትጠይቅ፤ ከሃጥያትህ ለመመለስና እውነት ለመከተል ወይም በጽድቅ ለመራመድ ተዘጋጅተህ ነው ወይ?
6. በቁ20-23 ገብርኤል ወደ ዳንኤል ሲመጣ ዳንኤል ምን እያደረገ ነበረ? ስለመጣበት ምክንያት መልዓኩ ለዳንኤል የነገረው ምንድነው? ዳንኤል ከገብርኤል የተቀበላቸው ሁለት ምክሮችስ ምንና ምንድናቸው?
7. በቁ1-3 እንደምናየው ዳንኤል መጸለይ የጀመረው እግዚአብሄር ምን እንዲያደርግ ነበረ? እግዚአብሄር በቁ24 ላይ የመለሰለት መልስ ከጥያቄው ጋራ ሲወዳደር እንዴት ታየዋለህ? ኤፌ 3፡20ን ከዚህ ጋራ በማነጻጸር ሃሳብ ተለዋወጡበት። የእግዚአብሄርን ቃል ተመርኩዞ በመጸለዩ ያገኘው መልስ አንተም ይህንኑ እንድታደርግ ምን ያህል ያበረታታሃል?
8. ቁ24 ‹‹… ስለህዝብህና ስለተቀደሰቸው ከተማህ ሰባ ሱባዔ ታውጇል›› ይህ አዋጅ የታወጀባቸውን ምክንያቶች አንድ በአንድ ዘርዝር። ቁ25 ሰባ ሱባዔና ሥልሳ ሁለት ሱባዔ የሚለው መቼ ተጀምሮ መቼ ነው የሚያልቀው? ዕዝ 1፡1 6፡3 7፡11 ነህምያ 2፡5 ከነዚህ ጥቅሶች መሃል አዋጁ የወጣበት የሚለው  የትኛውን አዋጅ ይመለልሃል? ለምን?
9. ዳንኤል በቤተ መንግስት ውስጥ እያገለገለ የሚገኘው ማንን ነው? ቁ17 ላይ በእግዚአብሄር ፊት ራሱን የሚያስተዋውቀው እንደማን አድርጎ ነው? አንተስ ሥራህ ዳቦ ከማስገኘት አልፎ የእግዚአብሄር ተልዕኮ ያለበት አገልግሎትህ እንደሆነ አምነህ ተቀብለሃል ወይ? የሥራህ ዓይነትና ባህርይ ምንም ይሁን ምን፤ በዚያ ሥፍራ እግዚአብሄርን የምትወክል የእግዚአብሄር አገልጋይ መሆንህን አትዘንጋ።

# ጥናት አስራ ሰባት ዳን 10፡1-11፡1

የጥናት ዓላማ፡- መልአኩ ገብርኤል ከሰይጣን ሰራዊት ጋራ ለመዋጋት የሚካአል እርዳታ ካስፈለገው፤ እኛ ከመላዕክት እጅግ ደካሞች የሆንን ሰዎች የጠላታችንን ሃይል ድል ለማድረግ ምን ያህል የቅዱሳን ድጋፍና እርዳታ እንደሚያስፈልገን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ነገር ግን የፋርስ መንግሥት አለቃ ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም በዚያ ከፋርስ ንጉስ ጋራ ተውሁት፡፡›› ዳን 10፡13

1. ዳን 10፡1-11፡1 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 መሰረት ዳንኤል ራዕዩን ያየበት ዘመን መቼ ነው? ራዕዩ ምንን በተመለከተ ነው? ስለመልዕክቱስ ዓይነት ይህ ክፍል ምን ይናገራል?
2. በቁ2-6 ላይ ዳንኤል ያየው ራዕይ በእርሱ ላይ ያስከተለው ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ዳንኤል ያየውን ሰው የገለጠባቸውን ሁኔታዎች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
3. ቁ7-9 ዳንኤል ራዕዩን ማየት ሲጀምር ሰው ከእርሱ ጋራ ነበረ ወይ? ሰዎች ከእርሱ ጋራ ነበሩ ካልን ራዕዩን ከእርሱ ሌላ ያየ ሰው ነበረ ወይ? በነዚህ ቁጥሮች ላይ የሆነው ነገር ከአዲስ ኪዳን የሚያስታውስህ የማንን ታሪክ ነው?
4. 9፡23 10፡11 10፡19 ላይ ስናነብ ለዳንኤል የተሰጠው አንድ ስያሜ ምን ነበረ? በነዚህ ሶስት ክፍሎች ይህንን ስያሜ ያገኘው ከማነው ብለህ ታምናለህ? ለምን? በመላዕክትና በተለይም ደግሞ በእግዚአብሄር ፊት ለአንተስ የሚሰጥህ ስያሜ ምን ይሆን ብለህ አስበህ ታውቃለህ?
5. በቁ12 አነጋገር ዳንኤል ቁርጥ የሆነ ውሳኔ ያደረገባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? የዳንኤል ጸሎት ከእግዚአብሄር ዘንድ መልስ የተሰጠው መቼ ነበረ? መልሱ ለእርሱ የደረሰው መቼ ነበረ? ዳንኤል መልሱ በእጁ እስኪገባ ድረስ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ? ከዚህ ለህይወትህ ምን ትማራለህ?
6. ቁ14-17 ትን በማንበብ ከመልአኩ መልዕክት ልንረዳ የምንችላቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? ዳንኤል ለምን ይመስልሃል መተንፈስ እንኳን እስኪያቅተው ድረስ የሆነው? ዳንኤል በዚህ ክፍል ስለህዝቡ የሚያሳየው አይነት ስሜት ለወገኖችህ በተለይም ቅዱሳን ይሰማሃል ወይ?
7. ቁ18-21 ዳንኤል እንደገና መልዓኩን መስማት የቻለው በምን ሁኔታ ነው? መልዕክተኛው በጦርነት ተመልሶ ሚካኤልን ለመርዳት ከመሄዱ በፊት ለዳንኤል መንገር የነበረበት ነገር ምን ነበረ?
8. በዚህ ክፍል ለዳንኤል መልዕክቱን ያመጣው ኢየሱስ እንደሆነ አንዳንዶች ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ ሊሆን አይችልም ብለው በማረጋገጥ ይናገራሉ፡፡ አንተ በየትኛው ሃሳብ ትስማማለህ? ለምን?
9. ወደ ቁ13 በመመለስ በዚህ ሥፍራ ሲካሄድ የምናየው ነገር ምንድነው? መልአኩ ገብርኤል ለዳንኤል የጸሎት መልስ ለማድረስ የቻለው በምን ሁኔታ እንደነበረ አስረዳ፡፡ መንፈሳዊ ውግያን ለማሸነፍ መልኩ የሌላ መልአክ እርዳታ ካስፈለገው፤ አንተስ መንፈሳዊ ውግያን ለመዋጋት የቅዱሳን ድጋፍ እንደሚያስፈልግህ ምን ያህል ገብቶሃል? መንፈሳዊ ውግያ ከሌሎች ቅዱሳን ጋራ በመረዳዳት የምታሸንፈው እንጂ ብቻዬን እወጣዋለሁ ብለህ መሞከር ሞኝነት እንደሆነ እወቅ፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት ዳን 11፡2-35

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄርን ማወቅ የጥበብ መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን፤ ጠላት ለማታለልና ለማሳት ወደእኛ የሚያመጣውን ሃሳብ ሁሉ ልንቃወምበት የሚያስችለን መሳሪያ ስለሆነ እግዚአብሄርን ማወቅ በህይወታችን ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባን ነገር እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹አምላካቸውን የሚያውቁ ህዝብ ግን ጸንተው ይቃወሙታል፤ እርምጃም ይወስዳሉ፡፡›› ዳን 11፡32

1. ዳን 11፡2-35 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ2 ላይ ከዳርዮስ በኋላ በፋርስ ላይ ስንት ነገስታት እንደሚነግሱ ነው መልዓኩ ለዳንኤል የሚነግረው? ስለአራተኛው ንጉስ የሚናገራቸውን ነገሮች በዝርዝር ተናገር፡፡
2. ቁ3ን ስናነብ የምናየው ንጉስ በፋርስ ላይ የሚነግስ ንጉስ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አብራራ፡፡
3. 7-20 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሰው የምናያቸው ሁለት ቃላት ምንና ምንድናቸው? በቁ16 ላይ ‹‹በመልካሚቱ ምድር ላይ ይገዛል›› የተባለለት የትኛው ንጉስ ነው?
4. በቁ21 ላይ ብቻ በመመሪኮዝ በሰሜን ማለትም በሶርያ ላይ ስለሚነግሰው ንጉስ ማንነት የምናውቃቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ከ22-24 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ይህ ንጉስ ስለሚያደርጋቸው ድርጊቶች የተነገሩትን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር፡፡
5. ቁ25-27 በዚህ ክፍል መሰረት የደቡቡ ማለትም የግብጽ ንጉስ በሰሜኑ ማለትም በሶርያ ንጉስ የተሸነፈበት ዋነኛው ምክንያት ምን ነበረ? ስለእነዚህ ሁለት ነገስታት በቁ27 የምናነበው ነገር ምንድነው? ይህ አይነቱን ድርጊት አንተስ ታስተናግደዋለህ ወይስ ትጸየፈዋለህ?
6. ቁ28-30ን ስናነብ የሰሜኑ ንጉስ ወደ አገሩ ሲመለስ እግረ መንገዱን ያደረገው ነገር ምን ታያለህ? በድጋሚ ደቡቡን ሊወር ሲመጣ የገጠመው ነገር ምን ነበረ? በደረሰበት ሽንፈት የተሰማውን ቁጣ የገለጠው ምን በማድረግ ነበረ?
7. ቁ31-32 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይህ ንጉስ የሚያደርጋቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር፡፡ ይህንን ንጉስና ሰራዊቱን የሚቃወሙና ጸንተው እርምጃ የሚወስዱትን ሰዎች ይህ ክፍል ምን በማለት ነው የሚጠራቸው? አንተስ ኪዳኑን ከሚተላለፉት እንዳትሆን ራስን ምን ያህል ታዘጋጃለህ?
8. ቁ33-35 ብዙዎችን እግዚአብሄርን ማወቅ የሚያስተምሩ ሰዎች በዚህ ክፍል አነጋገር ሊደርስባቸው የሚችሉት ነገሮች ምን ምንድናቸው? የእነዚህ ሰዎች ተማሪዎች በመሆን ከሚማሩት መሃል ምን ዓይነት ሰዎች እንደሚገኙ ነው ክፍሉ የሚነግረን?
9. በቁ32 ላይ ጸንተው የተቃወሙት ሰዎች ኪዳኑን እንዳይተላለፉና በማታለሉ እንዳይወሰዱ የረዳቸው አንድ ነገር ምን ነበረ? አንተስ እግዚአብሄርን ማወቅ ምን ያህል ዋነኛ ዓላማህ አድርገህ ትመላለሳለህ? እግዚአብሄርን ማወቅ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን፤ ከስህተትና ከመታለልም ሁሉ ልትጠበቅበት የምትችለው እንቁ ስለሆነ ከሙሉ ልብህ ልትከታተለው የሚገባህ ነገር ነው፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዳን 11፡36-12፡3

የጥናት ዓላማ፡- ሰዎችን ከዘላለም ጉስቁልና አድኖ ለዘላለም ህይወት ማብቃት በራሱ ትልቅ በረከት ሲሆን፤ በተጨማሪ እግዚአብሄር ደግሞ ብዙዎችን ወደ ጽድቅ ለሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም እንደሚደምቁ ተስፋ እንደሰጠ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ጥበበኞች እንደ ሰማይ ጸዳል፤ ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ፡፡›› ዳን 12፡3

1. ዳን 11፡36-12፡3 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዛሬ የተነበበው የትንቢት ቃል ከዳንኤል ዘመንና ከመጨረሻው ዘመን ስለየትኛው እንደሚናገር ይመስልሃል? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ?
2. ይህ ‹‹ንጉሱ›› በመባል በቁ36 ላይ ስለምናየው ሰው በዚሁ ቁጥር ውስጥ የተነገሩለትን ነገሮች ዘርዝር፡፡ ለምንድነው እግዚአብሄር ይህንን ሁሉ ማድረግ እንዲችል የሚፈቅደው?
3. ስለዚህ ሰው በቁ37-38 ውስጥ ተጨማሪ የምናነበው ነገር ምንድነው? ይህ ሰው ቦታ ከሚሰጣቸው ነገሮች መሃል በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህ ነገሮች ስለዚህ ሰው ምንን የሚያሳዩን ናቸው ብለህ ታምናለህ?
4. ቁ39 ላይ ስናነብ ይህ ሰው ጽኑ ምሽጎችን እንደሚወጋ ይነግረናል፡፡ ይህንን ለማድረግ ሃይሉን የሚያገኘው ከየት ነው? ከዚህ አይነቱ አነጋገር መረዳት የምንችለው ነገር ምንድነው? ይህ ሰው ለእርሱ ለሚገዙለት ሰዎች የሚያደርግላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡
5. ቁ40-43 ያለው ክፍል የሚናገረው ስለየትኛው ጊዜ ነው? ‹‹መልካሚቱ ምድር›› በመባል በዚህ ክፍል የተጠቀሰችው ሃገር ማን ነች?
6. ይህ ሃገሮችን ሁሉ እንደ ጎርፍ እየጠራረገ የሚያልፍ ሃይለኛ ንጉስ በቁ44-45 ላይ የሚያስደነግጠው ነገር ምንድነው? የዚህን ንጉስ መጨረሻ አስመልክቶ ከነዚህ ቁጥሮች የምንረዳቸው ነገሮች ምንድናቸው?
7. በ12፡1 በዚያን ዘመን ይሆናሉ ብሎ የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚፈጸሙት በማን ወይ ለማን ነው?
8. ቁ2 ትን ስናነብ ስለትንሳኤ ልንረዳ የምንችላቸው እውነቶች ምንድናቸው? ቁ2 ላይ ያለው ሃሳብና ቁ3 ላይ የምናነበው ሃሳብ በምን መንገድ ይገናኛል ብለህ ታምናለህ? ብዙዎችን ወደ ጽድቅ ለሚመልሱ የተገባላቸው ተስፋ ምን የሚል ነው? የሰዎች የዘላለም አድራሻ በአንተ እጅ መኖሩ ምን ያህል ገብቶሃል? ሰዎችን ከዘላለም ጉስቁልና አድኖ ለዘላለም ህይወት ማብቃት በራሱ ትልቅ በረከት ሲሆን፤ በተጨማሪ እግዚአብሄር ደግሞ ብዙዎችን ወደ ጽድቅ ለሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም እንደሚደምቁ ተስፋ ሰጥቷል፡፡

# <u>ጥናት ሃያ 12፡4-13</u>

የጥናት ዓላማ፡- ምንም እንኳን በጊዜው ጥያቄዎቻችን መልስ ባያገኙና ነገሮች ለእኛ ግልጽ ሆነው ባይታዩ፤ እግዚአብሄርን እስከፍጻሜ ይዘን ከተመላለስን በመጨረሻው የእረፍት ስፍራን እንደሚያወርሰን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድነው? ብዬ ጠየቅሁት…አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ ታርፋለህ፤ በቀኖቹም መጨረሻም ተነስተህ የተመደበልህን ርስት ትቀበላለህ፡፡›› ዳን 12፡8-13

1. ዳን 12፡4-13 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ4 ያለው ክፍል በአጠቃላይ በእስራኤላውያን ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ቁ4 ትኩረቱ በማን ላይ ነው? ዳንኤል በዚህ ቁጥር ላይ የታዘዛቸው ሁለት ትዕዛዞች ምንና ምንድናቸው? በዚህ ዘመን ይሆናሉ ተብለው የተነገሩትስ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
2. በቁ5-7 ላይ የምናየው እነማንን ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረበው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ለጥያቄው የተሰጠው መልስስ ምን የሚል ነው?
3. ዳንኤል ከጥያቄው መልስ የተረዳው ነገር ምንድነው? ዳንኤል ራሱ በቁ8 ላይ የጠየቀው ጥያቄ ምን የሚል ነው? ዳንኤል ለጠየቀው ጥያቄ የሚሆን መልስ አግኝቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. ‹‹ቃሉ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ስለሆነ ሂድ›› የሚለው አነጋገር ምን ማለት እንደሆነ ነው የሚገባህ?
5. ራዕይ 22፡10-11 ላይ ራዕዩን አስመልክቶ ለዮሐንስ የተሰጠው ትዕዛዝ ምን የሚል ነው? የተሰጠውስ ምክንያት ምን የሚል ነበረ? በዳን 12፡4 ላይ ለዳንኤል ከተሰጠው ትዕዛዝ እንዴት እንዴት እንደሚለይ አስረዳ፡፡ በራዕይ ላይ ያነበብነው ክፍል ከዳን 12፡9-10 ጋራ የሚመሳሰሉትን ሃሳቦች ተናገር፡፡
6. ቁ10ርን ስታነብ በመጨረሻው ወይም በፍጻሜው ዘመን ሰዎችን የሚከፍላቸው በምን ዓይነት ነው? እነዚህ ሰዎች አንዳቸው ከሌላቸው የሚለዩት በምንድነው? አንተስ በዚህ ዘመን ራስህን ከየትኛው ጋራ አሰልፈህ ትገኛለህ?
7. በቁ11-12 ላይ ለቀን ቆጠራው እንዲያገለግሉ ሆነው የተነገሩት ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? በአሁኑ ሰአት ቀኑን ለመቁጠር የሚያስችል ሁኔታ የለም ሊያሰኘን የሚችለው ነገር በአንተ አመለካከት ምንድነው ትላለህ? በዚህ ክፍል የተነገረውና በማቴ 24፡21 ላይ ኢየሱስ የተናገረው እንዲፈጸም አስቀድሞ መፈጸም የሚኖርበት ነገር ምንድነው?
8. የእግዚአብሄር ባሪያ በቁ8 ላይ ጥያቄ እንደጠየቀና መልስ እንዳላገኘ ተመልክተናል፡፡ በ13 ላይ ግን ስለራሱ መጨረሻ ጥያቄ እንዳይኖረው የተነገሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው? አንተስ ስለራስህም ሆነ በአካባቢህ ስለሚሆኑት ነገሮች ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉህ ወይ? ለጥያቄዎችህ ዛሬ መልስን ባታገኝም በእርሱ ላይ ታምነህ እስከ መጨረሻው በመሄድ አምላክህ እንደሚያሳርፍህና ያዘጋጀልህን ርስት እንደሚያወርስህ ቃል ተገብቶልሃል፡፡